ዲጂታል መጽሔት
ልዩ እትም



"አስተርአየ ዘኢያስተርኢ የማይታየው ታየ"

(ድጓ ዘዘመነ አስተርእዮ)

እግዚአብሔር ምስሌነ / Egziabher Meslene
WWW. Debregelila.org



ዋና አዘጋጅ

ኢሳያስ ጤናዬ
ልዲያ አቦወርቅ

አዘጋጅ

ምንተስኖት ደስታ
አምሳል ብርሃኑ

ግራፊክስና ሌዩ አውት

ይድነቃቸው መለሰ
(0989058258)

በማኅበራዊ መገናኛዎቻችን ቤተሰብ ይሁኑ!

የዩቲዩብ ቻናል፡
http://youtube.com/@EMislene

የቴሌግራም ቻናል፡
https://t.me/EMislene

የፌስቡክ ገጽ፡
https://www.facebook.com/EMislene/

የኢንስታግራም ገጽ፡
https://www.instagram.com/egziabher_meslene28/

የቲክቶክ ገጽ፡
https://www.tiktok.com/@egziabhermeslene28

ድሕረ ገጽ፡
www.debregelila.org

ነጋሪት

ማየ ሕይወት /የሕይወት ውሃ/

አብ ማየ ሕይወት ወልድ ማየ ሕይወት መንፈስ ቅዱስ ማየ ሕይወት ነው የሕይወት መሠረት ቅድስት ሥላሴ የሕይወት መገኛ ቅድስት ሥላሴ የሕይወት ምንጭ ቅድስት ሥላሴ ብለን እናምናለን እንታመናለን። ያለ ቅድስት ሥላሴ ስለ ሕይወት መናገር መመስከር አይቻልም። እግዚአብሔር ፍጥረታትን ካለመኖር ወደ መኖር / እምኀበ አልቦ ኀበቦ/ ያመጣበት ጥበቡ 4ቱ ባህርያት የፍጥረታት መሠረት እንደሆኑ መናገር የሚገባ ነው። ከአራቱ ባህርያት መካከል ውሃ የሕይወት አስገኝ የሕይወት መገኛ እንደሆነ የሐሙስ ሥነ ፍጥረት መመልከት በቂ ነው።

“የእግዚአብሔር መንፈስ በውሃ ሰፍሮ ነበር።” ይላል ዘፍ 1÷3 የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ከሆኑ ፍጥረታት መካከል አንዱ ውሃ ነው፡ ፡ ውሃ የሕይወት ምንጭ እራሱ አምላካችን ነው “ለተጠማ የሕይወት ውሃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ” ራዕ 20÷6 ይህ የሕይወት ውሃ ለተጠማ ሁሉ የሚሰጥ የሕይወት መጠጥ ይኸውም ልጅነት የምናገኝበት ጥምቀት ነው። የሚሰጠው ላመነ ወድዶ ፈቅዶ ለቀረበ ነው፡ ይህም የሕይወት ምንጭ ይሆንለታል። ጌታችን ለሳምራዊቷ እንደ ተናገረው “የሚለምንሽ ማን መሆኑን ብታውቂ አንቺ ራስሽ በለመንሽው ነበር” አላት “ዳግመኛ መጠማት የሌለበት የሕይወት ውሃ ከሆዱ ይፈልቃል” አላት “የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል” ይለናል ቅዱስ ጳውሎስ ገላ 3÷28፤ የክርስቶስን የልብሱን ጫፍ የዳሰሰች ሴት ለ12 ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረችው ከደዌው ፍውም ተፈውሳለች፤ እስቲ ልብ ብለን እናስተውል የልብሱን ጫፍ የነካችው እንዲህ ከተደረገላት የተጠመቅን ሁሉ ክርስቶስን ለብሰነዋልና ምን ያህል ዕድለኞች በብዙ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ የተዋሃድን መሆኑን ማስተዋል በጣም ይጠቅማል።

የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በጥምቀት በኩል የሚሰጠን በነፃ ፍቃድ ምሪት ሁል ጊዜ ዝንባሌአችን በጎ መልካም ከሆነ ብቻ ነው። ሰው ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት ራሱን ካዘጋጀ ሕይወቱን ሁሉ ለመልካም ሥራ ካዘጋጀ ምሪቱ በአሚነ ቅድስት ሥላሴ ካደረገ የሕይወት ውሃ ከሆዱ ይፈልቃል በእርሱ ክፉ ነገር በውስጡ ይሰለጥን ዘንድ አይቻለውም፤ ሥጋዊ ሆነ ደማዊ የሆነ የዚህ ዓለም ምኞት ፍቃድ ኃይላቸው ክብራቸው ኃላፊን ጠፊ ነው እንደ ጥላ ያሉና በራሳቸው ከንቱ ናቸው፤ ምንም ዓይነት ሥልጣኔ ቴክኖሎጂ ክርስትናን ሊተካ ሊወዳደር አይችልም ክርስትና ሕይወት - ሕይወትም ክርስትና ነው የሚመራው ቅዱስ መንፈስ እንጂ በሥጋ አስተሳሰብ መሠረትነት አይደለም። ምንም ዓይነት መንፈሳዊ የሚመስል ግን ከመንፈስ ቅዱስ ፈቃድና ሀሳብ ውጪ የሆኑ የዚህ ዓለም ፈቃድ ከሥጋዊነት ውጪ ሌላ ሊሆን አይችልም 12 ዓመት ደም ሲፈሳት የነበረች ሴት የልብሱን ጫፍ ብቻ በመንካት ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍሷ ፍጹም ፈውስን አግኝታለች የተጠመቅን ደግሞ ከዚህ የላቀ ጸጋ ተሰጥቶናል።

እግዚአብሔር ከፍጥረቶቹ መካከል ብቻ አይደለም ያደረገን ልጆቹ የርስቱ ተካፋይ አድርጎናል የተጠመቅን በልማድ ብቻ አይደለም ለሕይወት፣ ለመልካምነት፣ አማልክት ዘበጸጋ እንሆን ዘንድ ነው።

የተሰጠን ጸጋ በደንብ ካልተረዳነው የሕይወት አኗኗራችን ውስጥ የተገደበ በፈቃደ ሥጋ እና በመንፈሳዊ ሕይወት በሚመስል ውሉ በደንብ ያልታወቀ የእውነት መንገድ የሆነ የክርስትናን ጉዞ በትክክል ሊረዳ ያልቻለ ስለሚሆን በማስተዋል ሥጋዊነትና መንፈሳዊነት ልዩነቱ የለየ የጥንቃቄ ጉዞ መጓዝ የግድ ይለናል።

ማየ ሕይወት /የሕይወት ውሃ/ ከክርስቶስ ዐለት ውሃ መጠጣት ፈጽሞ ዳግመኛ መጠማት የሌለበት ነው። መውደቅ ቢኖር መነሣት አለ ስለዚህ መፍራት ማመንታት የለም ሁል ጊዜ ተስፋችን ከፊት እየሳበን ቸርነቱ ምሕረቱን ይዘን በጽናት መጓዝ ያስፈልጋል።

አስተርእየ ዘኢያስተርኢ — የማይታየው ታየ

(ድጓ ዘዘመነ አስተርእዮ)

መጋቤ ምሥጢር ፍሬ ስብሐት ዳባሰ
የሊቃውንት ጉባኤ ም/ሰብሰባ

መግቢያ

ዘጎቡእ እምጎቡኣን ወልዑል እምልዑላን ከተሠወሩት የተሠወረ፥ ከልዑላን በላይ ልዑለ ባሕርይ የሆነው አምላካችን እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ አስቀድሞ ባሕርዩን በባሕርዩ ሠውሮ የኖረ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስም ይህን ሲያስረዳ፦ «ወአስተርአየ በደኃሪ መዋዕል በእንቲኣነ — በኋለኛው ዘመን ስለእኛ ተገለጠ» በማለት። ቅድመ ዓለም ባሕርዩን በባሕርዩ ሠውሮ ይኖር የነበረ ስለእኛ (እኛን ለማዳን) የተገለጠ መሆኑን አስረድቷል። (1ጴጥ. 1፥20)

የማይታየው ፈጣሪ ዓለምን በመፍጠሩ ተገልጿል። ዓለምን ከፈጠረበት ጀምሮ በተለያየ ጊዜ በልዩ ልዩ ምሳሌ በፍጹም ሃይማኖት፥ በምስጋና፥ በጸሎት፥ በትሕትና፥ በንጽሕና፥ በቅድስና ሁነው ለሚሹትና ለሚፈልጉት ሁሉ በየጊዜው ተገልጿል።

በየጊዜው ሲገለጽም በራእይ፥ በሕልም፥ በአምሳል፥ በረድኤት በመሳሰለው ለወዳጆቹ የተገለጸላቸው ሲሆን፤ በኩነት የተገለጸው ግን በዘመነ ሥጋዌ ነው። ይህም በቅደም ተከተል እንደሚከተለው በዚህ ጽሑፍ በመጠኑ ተዳሷል። በመሆኑም፦

ዘመነ አስተርእዮ ምን ማለት ነው?
አስተርእዮ በጥንተ ፍጥረት
አስተርእዮ በማኅበረ መላእክት
አስተርእዮ በዘመነ አበው
አስተርእዮ በዘመነ መሳፍንት
አስተርእዮ በዘመነ ነገሥት
አስተርእዮ በትንቢተ ነቢያት
አስተርእዮ በዘመነ ሥጋዌ
አስተርእዮ በባሕረ ዮርዳኖስ

1) ዘመነ አስተርእዮ ምን ማለት ነው?

«ዘመነ አስተርእዮ» የሚለው ሐረግ ከሁለት የግእዝ ቃላት የተገኘ ሲሆን፤ «ዘመን» ማለት በቁሙ ዘመን፥ ዓመት፥ ሴኮንዶች ደቂቃዎችን፥ ደቂቃዎች ሰዓታትን፤ ሰዓታት ዕለታትን፥ ዕለታት ሳምንታትን፥ ሰምንታት ወራትን፥ ወራት ዘመንን ያስገኛሉ። አንዱ ዘመን ዘመነ መፀው፥ ዘመነ ሐጋይ፥ ዘመነ ጸደይ ዘመነ ክረምት ተብሎ በ4ት ተከፍሏል። ከአንዱ ዘመን ውስጥም ዘመነ ጽጌ፥ ዘመነ አስተምህሮ፥ ዘመነ ስብከት፥ ዘመነ ልደት፥ ዘመነ አስተርእዮ፥ ... ወዘተ. እየተባለ ተሰይሟል። ስለዚህ «ዘመን» የሚለውን ቃል የግእዝ መዝገበ ቃላት በቁሙ ዘመን፥ ዓመት፥ ጊዜ፥ ወራት በየስሙና በየክፍሉ ብሎ ተርጒሞታል። (መጽ.ሰዋ.ወግስ)

«አስተርእዮ» ማለት ደግሞ መታየት፥ መገለጥ ማለት ነው። ሁለቱ ቃላት ሲናበቡ «ዘመነ አስተርእዮ» የሚለውን ሐረግ ይሰጡናል፤ ዘመነ አስተርእዮ የሚለው ሐረግም ሲተረጐም የመታየት ዘመን፥ የመገለጥ ጊዜ ... ተብሎ ይተረጐማል። በሌላ ቃልም «ኤጲፋንያ» ወይም በጽርዕ «ሄፒፋንያ» የሚለውን ቃል በተመሳሳይ ትርጓሜ አስተርእዮ መታየት፥ መገለጥ፥ ዕለተ ጥምቀት በማለት ይተረጒመዋል። (መጽ.ሰዋ.ወግስ)

ቅዱሳን ሐዋርያትም በመጽሐፈ ዲድስቅልያ «ግበሩ በዓለ ኤጲፋንያ ዘውእቱ በዓለ ጥምቀት፥ ወይኩን በኀቤክሙ ክቡረ፥ እስመ ቦቱ ወጠነ እግዚእነ ከመ ያረኢ ስብሐተ መለኮቱ አመ ተጠምቀ በውስተ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ — የኤጲፋንያ (የአስተርእዮ) በዓልን አድርጉ፥ እርሱም በዓለ ጥምቀት ነው፤ በእናንተም ዘንድ የከበረ ይሁን። ጌታችን በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ በተጠመቀ ጊዜ የጌትነቱን ክብር ያሳይ ዘንድ ጀምሮበታልና» ሲሉ፥ የበዓሉን ታላቅነት ገልጸው ትእዛዝ አስተላልፈዋል። (ዲድስቅልያ አንቀጽ 9)

ስለዚህ ጌታ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ፥ አብ በደመና ላይ «የምወደው ልጄ ይህ ነው» ብሎ ሲመሰክርለት፥ መንፈስ ቅዱስም በራሱ ላይ በአምሳለ ርግብ ወርዶ ሲቀመጥ ምሥጢረ ሥላሴ የተገለጠበት ስለሆነ ዘመነ አስተርእዮ ተብሏል።

በመሆኑም ከዚህ አስቀድሞ ለወዳጆቹ በየጊዜው እንዴት ይገለጽላቸው እንደነበር በመጠኑ መግለጽ አስፈላጊ ይሆናል።

2) አስተርእዮ በጥንተ ፍጥረት

ዓለምን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የማይታይ የማይመረመር የነበረው ጌታ ዓለምን በመፍጠሩ ፈጣሪነቱ፥ ህልውናው፥ አምላክነቱ፥ ጌትነቱና ክብሩ በፍጥረቱ ለፍጥረቱ ታውቋል። ይህንንም ብርሃና ለቤተ ክርስቲያን የተባለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሲመሰክር «ወዘኢያስተርኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትዐወቅ በፍጥረቱ በሐልዮ ወበአእምሮ ወከመዝ ይትአመር ኀይሉ ወመለኮቱ ዘለዓለም — ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ታይቶ የማይታወቅ እግዚአብሔር የፈጠረውን ፍጥረት በማሰብና በመመርመር ይታወቃልና፤ ከሃሊነቱ፥ የዘለዓለም ጌትነቱም እንዲህ ይታወቃል» ብሏል። (ሮሜ 1፥20፤ መዝ. 08፥1)

ስለዚህ «ሥነ ፍጥረት» የመጀመሪያው የእግዚአብሔር መገለጥ መሆኑን በዚህ እንገነዘባለን።

3. አስተርእዮ በዓለመ መላእክት

የሥነ ፍጥረትን ምሥጢር አምልቶ አስፍቶ የጻፈው ኤጲፋንዮስ የተባለው የቤተ ክርስቲያን ሊቅ አክሲማሮስ በተባለው መጽሐፉ እንደገለጸው፥ ጌታ በመጀመሪያ ከፈጠራቸው ፍጥረታት ለባውያን ነባብያን ሁነው የተፈጠሩ ቅዱሳን መላእክት ናቸው። ጌታ እነርሱን ፈጥሮ ተሰውሯቸዋል። ትጉሃን መላእክትም በአእምሮ በለብዎ ተፈጥረዋልና፥ ማን ፈጠረን? ከወዴትስ መጣን? እያሉ ሲመራመሩ፥ አቡሃ ለሐሰት የተባለው ሐሰተኛው መልአክ ድምፃቸውን ሰምቶ ወደላይ ቢያዳምጥ የሚሰማው ድምፅ ቢያንጋጥጥም የሚያየው ገጽ ስለአጣ እኔ ፈጠርኳችሁ ... በማለት ለማሳሳት ሲሞክር መልአከ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል «አምላካችንን እስከምናገኘው ድረስ በያለንበት እንቁም (እንጽና)» ብሎ አጽንቷቸዋል።

በዚህ ጊዜ አምላከ ብርሃን እውነተኛው የብርሃን ጌታ እግዚአብሔር በብርሃን ተገልጾላቸዋል። «ወውእቱ ብርሃነ ኮኖሙ ጥበበ ወአእምሮ እንዳለው ሊቁ ... በዚህ ብርሃን አንድነቱን ሦስትነቱን ገልጾላቸው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ... ብለው አመስግነውታል።
(መቅ.ወን. አክሲማሮስ፥ ሥነ ፍጥረት)

4. አስተርእዮ በዘመነ አበው

ጌታ በዘመነ አበው በየዘመኑ ለአባቶቻችን በልዩ ልዩ ራእይ ተገልጿል። ይኸውም በገሃድ፥ በራእይ በሕልም በልዩ ልዩ አምሳል መገለጹን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። ለማስረጃም፡-

ለአባታችን ለአዳም በበደለ ጊዜ ለዘለፋ፥ ንስሓ በገባ ጊዜ ለውሂበ ተስፋ መገለጹ፥ (ዘፍ. 3፥9፤ መጽሐፈ ቀሌምንጦስ)

ለአቤል መሥዋዕት ባቀረበ ጊዜ መገለጹ (ዘፍ. 4፥4)፥ ለሄኖክ ወደ ደቂቀ ሴት በላከው ጊዜ መገለጹ፥

ለኖኅ ቅድመ ማየ አይኅ መርከብ እንዲሠራ ባዘዘው ጊዜ፥ ድኅረ ማየ አይኅ ኖኅ መሥዋዕት ባቀረበ ጊዜ መገለጹ፥ (ዘፍ. 6፥03፤ 7፥1፥ 9፥1፤2፥04)

ለአብርሃም በተደጋጋሚ መገለጹ፤ ይልቁንም በአምሳለ እንግዳ በቤቱ (በድንኳን) ማረፉ፥ (ዘፍ. 02፥1)

ለይስሐቅ መገለጹ፥ (ለያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ መገለጹ በመጽሐፍ ቅዱስ የተመከረ ሐቅ ነው፥

ቀደምት አበው እግዚአብሔር አምላክ በልዩ ልዩ ራእይ፥ ሕልም፥ አምሳል እየተገለጸላቸው ያለ ምንም መምህር እርሱን ሲያመልኩ ኑረዋል። ድምፁን ሰምተዋል፤ ቃል በቃልም ተነጋግረዋል።

5. አስተርእዮ በዘመነ መሳፍንት

ከዘመነ አበው ቀጥሎ ያለው ዘመነ መሳፍንት ይባላል። ጌታ ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ ምድር ሲወጡ ጀምሮ መንፈሳዊ ምግብናውን ለካህን፥ ሥጋዊ አስተዳደሩን ለመስፍን ሰጥቶ፥ ካህን ሲሞት ካህን፥ መስፍን ሲሞት መስፍን እየተካ ለብዙ ዘመናት መርቷቸዋል። በዚያ ዘመንም በተለያየ ራእይ በየዘመኑ እየተገለጸላቸው ሲመራቸውና ሕጉን፥ ትእዛዙን ሲገልጽላቸው ኑሯል። ለዚህ ማስረጃ በመጠኑ ለማሳየት ያህል፡- ለመጀመሪያው መስፍንና ሊቀ ነቢያት ሙሴ በተለያየ ጊዜ፥ በተለያየ ራእይ መገለጹ፣ለኢያሱ፣ለጌዴዎን፣ ለዮፍታሔ፣ ለሳሙኤል... ለመሳሰሉት ሁሉ መገለጹን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ።

6. አስተርእዮ በዘመነ ነገሥት

ከዘመነ መሳፍንት ቀጥሎ ያለው ዘመን፥ ዘመነ ነገሥት ይባላል። በዚህ ዘመን፥ ንጉሠ ነገሥት፥ እግዚአ አጋእዝት፥ መኰንነ ኵሉ ፍጥረት የተባለው አምላካችን እግዚአብሔር በልዩ ልዩ መገለጥ ታይቷል። ይኸውም፡-

ሥርወ መንግሥት ለተባለው ለንጉሥ ዳዊት መገለጡ፥ ይህ ልበ አምላክ የተባለው ነቢዩና ንጉሡ ዳዊት «ዘልፈ እሬእዮ ለእግዚአብሔር ቅድሜየ ውእቱ በኵሉ ጊዜ እስመ በየማን ውእቱ ከመ ኢይትሀወክ ለዓለም — ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ በቀኜ ነውና አልተውክም» በማለት እግዚአብሔር የተገለጠለት መሆኑን ገልጿል፥ (መዝ. 05፥8)

ለጥበበኛው ንጉሥ ለሰሎሞን መገለጹ፥ (ነገ.ቀዳ. 3፥5)

ለሌሎችም አበው ቀደምት ነገሥት በየጊዜው በገሃድ፥ በራእይ፥ በሕልም፥ በረድኤት፥ በተአምራት በመሳሰለው ሁሉ ተገልጧል።

7. አስተርእዮ በዘመነ ነቢያት

አስተርእዮ በዘመነ ነቢያት የሚለው ንኡስ ርእስ እጅግ ብዙ መጠነ ሰፊ ዳሰሳ የሚያስፈልገው ነው። ምክንያቱም ጌታ ለቅዱሳን ነቢያት በየዘመናቸውና በየጊዜያቸው በተለያየ ምሳሌ ያልተገለጸለት ነቢይ የለም። የጸፉትም እርሱ የገለጸላቸውንና ያናገራቸውን ነው። በዚህ ጽሑፍም በመጠኑ ለማሳየት ያህል፡-

ልዑለ ቃል ለተባለው ነቢይ ለኢሳይያስ (ኢሳ. 6፥1-7)፥

ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለመረጠው ለነቢዩ ኤርምያስ፥ (ኤር. 1፥4-9)

ለነቢዩ ሕዝቅኤል በፈለገ ባሕር፥ (ሕዝ. 1፥1-8)

በባዕድ ሀገር ሁኖ አምልኮቱን አጽንቶ ለኖረው ዳንኤል፥ (ዳን. 7፥9)

በመሳሰለው ሁሉ በየጊዜው ለወዳጆቹ ተገልጿል።

ይህ ሁሉ አስተርእዮ የተስፋ፥ የረድኤት፥ የተአምራት፥ የትንቢት፥ የራእይ፥ የሕልምና የመሰለው አስተርእዮ ነው። ዋናውና አማናዊው አስተርእዮ የተስፋውና የትንቢቱ ፍጻሜ ሲደርስ በዘመነ ሥጋዌ የተደረገው አስተርአዮ ነው።

8. አማናዊ አስተርእዮ በዘመነ ሥጋዌ

«እግዚአብሔር እግዚእ አስተርአየ ለነ ግበሩ በዓለ በትፍሥሕት በኀበ እለ ያስተሐምምዎ ... ጌታ እግዚአብሔር ተገለጸለን፥ በዓልን በደስታ አድርጉ ...» በማለት ነቢዩ ዳዊት እንደተናገረው፥ የእግዚአብሔር መገለጥ በብሉይ ኪዳን ምን እንደሚመስል፥ ማለትም በረድኤት፥ በተስፋ ድኂን፥ በምሳሌ፥ በትንቢት፥ በራእይ፥ በሕልም፥ በገሃድ ... በመሳሰለው ሁሉ እንዴት እንደተገለጸ በመጠኑ አይተናል።

ይህ ሁሉ በተስፋ ሲጠበቅ የነበረው ጊዜ ሲደርስ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደ ዓለም ላከ፤ ይህንም ብርሃና ለቤተ ክርስቲያን የተባለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፡- «ወአመ በጽሐ ዕድሜሁ ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ ወተወልደ እምብእሲት ወገብረ በሕገ ኦሪት — ቀጠሮው በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ላከ፥ ከሴትም ተወለደ፤ በኦሪት የታዘዘውንም ፈጸመ» (ገላ. 4፥4፤ ኤፌ. 1፥0)

ይህ በቀጠሮው ጊዜ የተፈጸመው ተስፋ አበው የጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ከሰማይ መላእክትን፥ ከምሥራቅ እጅ መንሻ የሚያቀርቡ ነገሥታትን፥ ከቅርቡ መንጋቸውን የሚጠብቁ ኖሎትን (እረኞችን) በአንድ አሰባስቦ በተአምራት በብርሃን ስቦ አንድ መዝሙር እንዲዘምሩ አደረገ። (ሉቃ. 2፥6)

በዚህ ጊዜ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ፥ ነገሥተ ተርሴስ ወደሰያት አምኃ ያበውኡ ነገሥተ ሳባ ወዐረብ ጋዳ ያምጽኡ ወይሰግዱ ሎቱ ኵሎሙ ነገሥተ ምድር — በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ፤ ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ፥ የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ፤ የሳባና የዐረብ ነገሥታት እጅ መንሻ ያቀርባሉ፤ ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል» ሲል የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ (ማቴ. 2፥1-02)። ቅድስት ሀገራችን ኢትዮጵያውም የዚሁ አማናዊ አስተርእዮ በረከት ተካፋይ ሁናለች። ቀድሞ ንግሥተ ሳባ ለሰሎሞን ንጉሥ ገጸ በረከት እንደሰጠችው እውነተኛው ንጉሥ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜም የኢትዮጵያው ንጉሥ ባዜን እጅ መንሻውን ለጌታ ካቀረቡት ነገሥታት አንዱ እንደነበረ አበው ሊቃውንት በትርጓሜ ዳዊት ገልጸዋል። (መዝ. 71፥9-11)

9. አስተርእዮ በፈለገ ዮርዳኖስ

እንዲህም አድርጎ «በበሕቅ ልህቀ በ# ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ ...» እንዲል በየጥቂቱ አደገ፤ ዓመት ሲሞላው በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠመቀ።

ኮከበ ሊቃውንት፥ ጥዑመ ልሳን ቅዱስ ያሬድ ይህን አስተርእዮ ሲሰብክ «ሐዳፌ ነፍስ ለጻድቃን ቀተስፋ ቅቡጻን ክርስቶስ አስተርአየ ውስተ ዓለም እምድንግል ተወልደ ክሡተ ኮነ እንዘ ይትኤዘዝ ለአዝማዲሁ ከዊኖ ሰብአ በዮርዳኖስ ተጠምቀ — ነፍሳትን የሚያሻግር፥ ተስፋ ለቆረጡት ተስፋቸው ክርስቶስ በዓለም ተገለጠ፤ ከድንግል ተወለደ፥ ለዘመዶቹ ሲታዘዘ ተገልጦ ታየ፥ ሰው ሁኖ በዮርዳኖስ ተጠመቀ» በማለት ይሰብከዋል። (ድጓ ዘዘመነ አስተርእዮ)

ስለዚህ በፈለገ ዮርዳኖስ ስለተፈጸመው አማናዊ አስተርእዮ ነቢዩ ዳዊት አስቀድሞ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ገልጾለት «ባሕርኒ ርእየት ወጎየት ወዮርዳኖስኒ ገብአ ድኅሬሁ — ባሕርም አይታ ሸሸች፤ ዮርዳኖስም ወደኋላው ተመለሰ» በማለት ዘምሯል። (መዝ.3፥3)

ማጠቃለያ

ከላይ በርእሱ እንደተገለጸው ታላቁ የዜማ አባት ኢትዮጵያዊው የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ይህ የመገለጥ በዓል እንደሚከተለው ገልጾታል «አስተርአየ ዘኢያስተርኢ ኮነ እሙነ አስተርእዮቱ ለመድኀኒነ ክርስቶስ — የማይታየው ታየ፤ የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መታየቱ እውነት ሆነ። በማለት ስለዚህ ታላቅ የመገለጥ በዓል ዘምሯል (ድጓ ዘአስተርእዮ)፤ ይህንም እንዲሁ ከልቡናው ብቻ አቅንቶ አልተናገረም፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር መገለጥ የተጻፈውን መሠረት አድርጎ እንጅ።



ስለዚህ የአስተርእዮ (የመገለጥ በዓል) ከላይ በመጠኑ እንደተገለጸው አስቀድሞ ትንቢት ተነግሯል፥ ምሳሌ ተመስሏል። ልበ አምላክ የተባለው ነቢዩ ዳዊትም ስለዚህ በዓል፦ «ርእዩከ ማየት እግዚኦ፥ ርእዩከ ማየት ወፈርሁ ደንገፁ ቀላያተ ማያት ወደምፃ ማያቲሆሙ — አቤቱ ውኃዎች አዩህ፥ ውኃዎችም አይተው ሸሹ፤» ብሏል። ይህም በብሉይ በሙሴ ዘመን በባሕረ ኤርትራና በኢያሱ ዘመን በባሕረ ዮርዳኖስ የተፈጸመውን ድንቅ ተአምር የሚያስረዳ ሲሆን፤ በሐዲሱ ሲተረጐም ደግሞ ጌታ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ የተፈጸመውን ድንቅ ተአምር ያስረዳል። (መዝ. 76፥6)

ሐዋርያውም እግዚአብሔር ለምን (ስለ ምን) እንደተገለጸ ሲያስረዳ «ወበእንተ ዝንቱ አስተርአየ ወልደ እግዚአብሔር ከመ ይስዐር ግብሮ ለሰይጣን ... ስለዚህ ነገር የሰይጣንን ሥራ ይሽር ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» ብሏል። (1ዮሐ. 3፥8)

ከዚህ ከሐዋርያው ትምህርት እንደምንረዳው ይህ የአስተርእዮ (የመገለጥ) በዓል፦

1)ይህ በዓል እግዚአብሔር ወልድ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ በትሕትና ሲጠመቅ የታየበት የትሕትና በዓል ነው፥

2)ይህ በዓል እግዚአብሔር አብ በደመና ሁኖ «የምወደው ልጄ ይህ ነው ...» ብሎ ፍቅርን የሰበከበት የፍቅር በዓል ነው፥

3)ይህ በዓል እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ በራሱ ላይ ወርዶ ሲቀመጥ የታየበት፥ በዚህ ዕለት በቅንነት ላገለገለ ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በሰፊው የሚገኝበት፥ ... በአጠቃላይ ምሥጢረ ሥላሴ በገሃድ የተገለጠበት የነገረ ድኅነት መሠረት፥ የመንግሥተ ሰማያት መግቢያ በር የሆነችው ምሥጢረ ጥምቀትን ጌታ በተግባር የፈጸመበት (ያስተማረበት) ዕለት ስለሆነ በዓሉ እጅግ ታላቅ በዓል ነው።


በዓለ አስተርእዮ የመገለጥ በዓል ስለሆነም ታቦተ ሕጉ ከቤተ እግዚአብሔር ወደ ጥምቀተ ባሕር ወርዶ፥ በካህናት በሊቃውንት፥ በመዘምራንና በምእመናን ታጅቦ ከባሕረ ጥምቀቱ ሲደርስ በተዘጋጀለት ድንኳን ያድራል።

ለበዓሉ የሚገባው አገልግሎት ሲፈጸም አድሮ ቅዳሴ ከተቀደሰ በኋላ ባሕረ ጥምቀቱ ይባረካል። ባሕረ ጥምቀቱ ተባርኮ ሕዝቡ ከተጠመቀ በኋላ ታቦተ ሕጉ በከፍተኛ ድምቀት በያሬዳዊ ዜማና በልዩ ልዩ አገልግሎት ታጅቦ ወደ መንበረ ክብሩ ይመለሳል።

በዚሁ በዘመነ አስተርእዮ ከሚከበሩ በዓላት መካከል የእመቤታችን የዕረፍቷ በዓል «አስተርእዮ» ይባላል።

በጥምቀቱ ውኃን ለጥምቀታችን የቀደሰልን አምላካችን ይክበር ይመስገን፤ አሜን።

መጋቤ ምሥጢር ፍሬ ስብሐት ዳባሰ
የለቃውንት ጉባኤ ም/ሰብሳቢ



አትሮንስ

“የተጠመቃችሁ እናንተ ሁላችሁ ክርስቶስን ለብሳችኋል” ገላ 3÷27

በቀሲስ ኃይለኪየሱስ ተመስገን

የመጀመርያው ሰው አዳምን እግዚአብሔር በአርአያውና በአምሣሉ ከመፍጠር አልፎ በሥነ ፍጥረቱ ላይ ከሱ በታች በሰጠው የገዢነት ሥልጣን ፍጹም ፍቅሩን ገልጾለታል። “የባህር ዓሳዎችን፣ የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትን ሁሉ ይግዛ” ዘፍ 1÷26

ይህ ከፍጥረታት ሁሉ በላይ ከፈጣሪ በታች የከበረው አዳም (የሰው ልጅ) ከትእዛዘ እግዚአብሔር አፈንግጦ በምክረ ዲያቢሎስ ተታሎ “እንዳትበላ” የተባለውን ዕጸ-በለስ በመብላቱና ሕጉን በመተላለፉ ምክንያት የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ከእግዚአብሔር ልጅነት ተለይቶ ይኖር ነበር ዘፍ 2÷16-18

ስለዚህም ከሦስቱ አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ የሰውን በኃጢአት መተዳደፍና መውደቅን ተመልክቶ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በኅቱም ድንግልና ተጸንሶ በኅቱም ድንግልና ተወለደ:: እስከ ክርስቶስ ልደት የነበረው የሰው ልጆች ልደት ሁሉ ገና በማኅጸን ሳለ የአዳምና የሔዋን ርግማን የሚያገኘው በመርገም በፍዳ የሚያዝ ነበር። ቀዳማዊውን አዳም ከመርገም፣ ከዘለዓለም ሞት ያድን ዘንድ ዳግማዊ አዳም ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ግን ሰውን ሁሉ ያገኝ የነበረው መርገም አላገኘውም። ቀዳማዊው አዳም ገበሬ ካልጋረባት፣ ማረሻ ካልዘረባት፣ ዘር ካልወደቀባት ምድር እንደተፈጠረ ዳግማዊው አዳም ኢየሱስ ክርስቶስም መርገም (ጥንተ አብሶ) ካላገኛት በመንፈስ ቅዱስ ግብር በውስጥ በአፍአ፣ በነፍስ በሥጋ ንጽሕት ድንግል ከሆነች ከእናታችን ከድንግል ማርያም ያለ ዘርዓ ብእሲ ተወለደ። ይኽውም “ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ። እግዚአብሔር በመካከልዋ ነው አትናወጥም።” የተባለው ይፈጸም ዘንድ ነው ኢሳ 1፥9 መዝ 45፥4

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደው ለሰው ልጅ ድኅነት ነው። አዳም በተሰደደበት ምድር ተመላልሶ የጠፋውን ለመፈለግ፣ ከመንጋው ተለይቶ የባዘነውን ወደ መንጋው አንድነት ለመመለስ፣ በጨለማ ውስጥ ለወደቀው ብርሃን ለመሆን፣ የተራበውን ኅብስተ ሕይወት ለመመገብ የተጠማውን ከሕይወት ውሃ ለማጠጣት፣ የወደቀውን ለማንሳት ነው።

በዚህ ልደት የሰው ልጅ የተለያዩ አምላካዊ በረከቶችን አግኝቷል። የሰው ልጅ ኃጢአት ሠርቶ እግዚአብሔር ከገነት ካስወጣው በኋላ መላእክት እንዳይገባባት ገነትን በእሳት ሰይፍ ይጠብቋት ነበር ዘፍ 3፥22 በክርስቶስ ልደት ግን “ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ” እያሉ አብረው ዘመሩ በአንድነት ሰው የሆነውን አምላክ አመሰገኑት።በክርስቶስ ልደት ዕርቅ ተጀምሯልና ሉቃ 2÷14 ለእናቱ ለቅድስት ድንግል ማርያም እንደ ልጅነቱ እየታዘዘ አደገ። ከሦስቱ አካል አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት ተወስኖ ከድንግል ማርያም ቢወለድም እርሱ የጌቶች ጌታ የነገሥታት ንጉሥ የአማልክት አምላክ ነው ራዕ 17÷14፤ ራዕ 19÷16፤ ዘዳ 10÷17 1ኛጢሞ 6÷15

የጥምቀት ትርጉም

ጥምቀት ማለት “አጥመቀ” ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን አጠመቀ ማጥመቅ መጠመቅ የሚል ትርጉም የሚሰጥ ቃል ነው። ጥምቀት ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ በተጸለየበት ውሃ አንድም ማየ ገቦ ውስጥ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም መጥለቅ፣ መዘፈቅ፣ መነከር ማለት ነው። ጥምቀት በድርእ ቋንቋ ኤጲፋኒ ይባላል። በአማርኛ መገለጥ የሚል ትርጉም አለው።

ይህም የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት ምሥጢር በባሕረ ዮርዳኖስ በገሃድ የተገለጠበት በመሆኑ ነው። ጥምቀት የሥላሴ ልጅነት የሚሰጥበትና የኃጢአት ሥርየት የሚገኝበት ምሥጢር ነው።

ጥምቀተ ክርስቶስ

“የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ” ማቴ 3፥2 እያለ በይሁዳ ምድረ በዳ ያስተምርና ሕዝቡንም ንስሐቸውን እየተቀበለ ያጠምቃቸው የነበረው አጥማቂው ቅዱስ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ሳለ በዘመነ ሉቃስ በዕለተ ማክሰኞ ሌሊት 10 ሰዓት ላይ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊጠመቅ ሲመጣ በሩቅ ባየው ጊዜ “እኔ ባንተ ልጠመቅ እሻለሁ አንተ ወደ እኔ ትመጣለህ?” ብሎ ተናገረው ጌታችን ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው “አሁንስ ፍቀድልኝ ጽድቅን ልንፈጽም ይገባናልና” አንድም አንተም መጥምቀ መለኮት ተብለህ ክብርህ ይነገራልና እኔም በፍጡሩ የተጠመቀ ትሁት አምላክ ስባል እኖራለሁ አለው። ከዚህ በኋላ ቅዱስ ዮሐንስ ጌታን “ ጌታ ሆይ ሌላውን ሰው በአንተ ስም በባሕርይ አባትህ በአብ ስም በባሕርይ ሕይወትህ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠምቃለሁ አንተን የማጠምቀው በማን ስም ነው ብሎ ጠየቀው” “ወበ ስመ ሙኑ አጠምቅ ኪያከ” እንዲል። ጌታም እንዲህ አለው “ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢያተ ዓለም ውሉዱ ለቡሩክ ከሳቴ ብርሃን ተሣሃለነ አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከጼዴቅ” ትርጉም፡ - እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ብርሃን የሚገልጥ የቡሩክ ልጅ ይቅር በለን አንተ እንደ መልከጼዴቅ ክህነት ለዓለም ካህን ነህ። እያልክ አጥምቀኝ አለውና ከውኃው ሲገባ ዮርዳኖስ ወደ ኋላ ሸሸች ጌታም ባለችበት አጸናት። ለጌታ ሠላሳ ዘመን ሲሞላው ለዮሐንስ መንፈቅ ሲያልፈው በፈለገ ዮርዳኖስ ለዮሐንስም እንደነገረው “ውሉዱ ለቡሩክ ከሳቴ ብርሃን.....” እያለ አጥምቆታል። አገልጋዩ ቅዱስ ዮሐንስም አካላዊ ቃልን በማጥመቁ “መጥምቀ መለኮት” ተብሎ ክብሩ ሲነገር ይኖራል።

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ልጅ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ከውሃ ወጣ ሰማይም ተከፈተ የእግዚአብሔር መንፈስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀመጠ እነሆም ወመጽአ ቃል እም ሰማይ ዘይብል “ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር” በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው የሚል ድምጽ ከሰማይ መጣ በዚህም የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት ምሥጢር ተገለጠ ሉቃ 3፥21 ፣ ማቴ 3፥17 እዚህ ላይ ሌላው ልብ ልንለው የሚገባን መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል የወረደው ጌታ ከውሃ ከወጣ በኋላ ነው እንጂ ውሃው ውስጥ ሳለ አይደለም ይህስ ለምን ሆነ ካልን ምሥጢሩ እንዲህ ነው። በወቅቱ የነበሩት ሕዝቦች ዮሐንስን ያከብሩት ነበርና ጌታ በውሃ ውስጥ ከዮሐንስ ጋር ባለበት ሰዓት ወርዶ ቢሆን መንፈስ ቅዱስ ለዮሐንስ እንጂ ለጌታ አይደለም ባሉ ነበር። አንድም ውሃን የሚባርክ መልአክ እንዳለ ያውቁ ነበርና ውሃውን ለመባረክ መጣ እንጂ ለጌታ ነው ባላሉ ነበርና። አንድም ማረፊያ ያጣች ርግብ በባሕር ስትበር አረፈችብት ይሉ ነበርና ይህንን ሐሰባቸውን ያጠፋ ዘንድ ጌታ ከውሃ ውስጥ ከወጣ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወረደ።

ጌታችን የተጠመቀበት ምክንያት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እከብር አይል ክቡር፤ እነግሥ አይል ንጉሥ ሲሆን ስለምን ተጠመቀ ቢሉ ጌታችን የተጠመቀው እኛ ተጠምቀን ልጅነትን እንደምናገኘው ልጅነትን ለማግኘት አይደለም። ምክንያቱም

ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ጌታችን ከባሕርይ አባቱ ከአብ ተወልዷልና መዝ 2÷7 ምሳ 8÷23-25 ቀዳማዊ ልደት የሚባለው ከፍጥረት በፊት ጊዜያት ሳይፈጠሩና ሳይፈራረቁ ወልድ ከአብ ያለ እናት መወለዱ ነው። ደኃራዊ(ሁለተኛ) ልደቱ ደግሞ የወልድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት መወለዱ ነው። ስለዚህ ጌታችን የተጠመቀው ልጅነትን ለማግኘት አልያም ዋጋ ክብር ሽቶ ሳይሆን የአንድነትና የሦስትነቱ ምስጢር እንዲገለጥ፣ ውኃውን ለመቀደስ፣ የአዳምና የሔዋንን የዕዳ ደብዳቤ ለመደምሰስና በዲያብሎስ የስህተት ምክር ተታሎ የጠፋውን የአዳምን የልጅነት ክብር ለመመለስ መሆኑን እንረዳለን።

ጥምቀት በምሥጢረ ሥላሴ እና በምሥጢረ ሥጋዌ አምኖ ለሚቀበል ሰው ሁሉ ለኃጢአት መደምሰሻ ከእግዚአብሔር የፀጋ ልጅነትን ለመቀበል የተሰጠ የሕይወት መንገድ ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት መሠረት ከአምስቱ አዕማደ ምሥጢራት አንዱና ከሁሉም የሚቀድም የሕይወት መግቢያ በር ነው። በጥምቀት ከእግዚአብሔር እንወለዳለን። ከእግዚአብሔር መወለዳችንም የእግዚአብሔርን ርስት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ ነው። ጌታ ለምን ተጠመቀ ቢሉስ ቀድሞ በልደቱ ብርሃነ መለኮቱን ገልጦ በሰውና በእግዚአብሔር፣ በሰውና በመላእክት ዘንድ እርቅ መስርቶ ሰውና መላእክት በአንድነት "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ" እያሉ እንዲዘምሩ ያደረገ ወልደ እግዚአብሔር ዳግመኛ በጥምቀቱ የሦስትነቱን ምሥጢር ይገልጥልን ዘንድ ነው፡ ፡ አንድም በእርሱ ጥምቀት የእኛን ጥምቀት ሊባርክልንና ለአርኣያ ለትምህርት እንዲሆነን፣ በዮርዳኖስ ተጥሎ የነበረውንም የእዳ ደብዳቤ ሊደመስስልን ጌታ ተጠመቀ።

ጌታችን የመሠረታት ጥምቀት ኃጢአትን የምታስተሰርይና ድኅነትን የምታሰጥ ናት። ጌታ ራሱ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" ማር 16፥16 ብሏልና። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በበዓለ ሃምሳ ለተሰበሰቡ ሰዎች "ንስሐ ግቡ ሁላችሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ኃጢአታችሁም ይሰረይላችኋል የመንፈስ ቅዱስም ጸጋ ትቀበላላችሁ" ሐዋ 2፥30 ብሎ መክሯቸዋል። 318ቱ ቅዱሳን አበውም በጸሎተ ሃይማኖት ላይ "ኃጢአት በሚሰረይባት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን" ብለው አስረግጠው ተናግረዋል ።

ጌታ የተጠመቀው፡-

የዕዳ ደብዳቤያችንን ለመደምሰስ ነው፡- ብዙ ወንዞች ሳሉ ዮርዳኖስን መምረጡ የዕዳ ደብዳቤያችንን ሊያጠፋ ነው። ዲያቢሎስ በአባታችን አዳም እና በእናታችን ሔዋን ላይ የጨለማ መጋረጃ ጋርዶ "ስመ ግበርናታችሁን ጽፋችሁ ብትሰጡኝ አገዛዝ ባቀለልኩላችሁ ነበር" አላቸው በዚህ ጊዜ "አዳም ገብሩ ለዲያቢሎስ ሔዋን አመቱ ለዲያቢሎስ" ብለው ጽፈው ሰጡት። ከዚያ በሁለት እብነ ሩካም (ድንጋይ) ቀርጾ አንዱን በዮርዳኖስ ሁለተኛውን በሲያል ጥሎት ነበር። በዮርዳኖስ የጣለውን በጥምቀቱ በሲያል የጣለውን በዕለተ ዓርብ በአካለ ነፍሥ ወርዶ አጥፍቶልናል በዚህ ምክንያት ጌታ በዮርዳኖስ ባሕር ተጠመቀ ቆላ 2፥14

ምሥጢሩ ይገለጥ ዘንድ ነው፡- ጌታ በተጠመቀ ጊዜ ለሰው ልጆች በገሃድ ያልታወቀው ረቂቅ ምሥጢር ተገልጧል። እርሱም ምሥጢረ ሥላሴ የእግዚአብሔር የአንድነት የሦስትነት ምሥጢር ነው። አብ በደመና "ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ሎቱ ስምእዎ" በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ ሲመሰክርለት መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል በራሱ ላይ አረፈ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ቆሞ ታየ (ተጠመቀ) ማቴ 3÷16-17 ማር 2÷9-11 ሉቃ 3÷21-22 በዚህ ጊዜ የምሥጢረ ሥላሴ አንድነትና ሦስትነት በገሃድ ሊታወቅ ችሏል። ወቅቱም የመገለጥ ዘመን /ዘመነ አስተርዕዮ/ እየተባለ ይጠራል።

ለአብነት (ለምሳሌ) ነው፡- "እኔ ለእናንተ እንዳደረኩ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሣሌ ሰጥቻችኋለሁ" ዮሐ 13÷15 1ኛጴጥ 2÷21 ሲል ራሱ ጌታችን እንደተናገረ እርሱ ተጠምቆ እናንተም ተጠመቁ ለማለትና ለእኛ አብነት ሊሆነን ተጠመቀ።

ትህትናን ለማስተማር ነው፡- "እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝና" እንዳለ አምላክ ሲሆን በእሩቅ ብእሲ እጅ ተጠመቀ ይህም ትህትናውን ለመግለጥ ነው።
የእኛን ጥምቀት ለመባረክረና ለመቀደስ ነው።

የጌታችን በሠላሳ ዘመን መጠመቅ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በዘመነ ሉቃስ በወርሃ ጥር አሥር ቀን ማክሰኞ ሌሊት አሥር ሰዓት ነበር። ፍትሐ ነገስት አንቀጽ 19። በተጠመቀ ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበር። በብሉይ ኪዳን ሥርዓትና ልማድ ካህናት ለቤተክርስቲያን ተልዕኮና ለመንፈሳዊ አገልግሎት ከሠላሳ ዓመት ዕድሜ በፊት አደባባይ አይወጡም ነበር፡ ፡ እጅግ አሰፈላጊ እንኳን ቢሆን ከሃያና ከሃያ አምስት ዓመት ዕድሜ አስቀድሞ ለአገልግሎት መሰየም ልማድ አልነበረም። የቤተክርስቲያን አገልጋዮች በዕድሜና በዕውቀት የበሰሉ፣ በጠባይና በሥራ ልምድ የተፈተኑ፣ ተልኪቸውን በብቃት ለመወጣት በተገልጋዩ ሕዝብ ዘንድ የተመሰከረላቸው መሆን ነበረባቸው። 1ኛዜና 23÷24 ዕዝ 3÷8 1ኛጢሞ 3÷1-10 ዘኁ 4፥3 ያንን ሥርዓት ለመፈጸም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው በሠላሳ ዓመቱ ነበር። መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስም የጌታን መምጣት ለማወጅ በዮርዳኖስ በይሁዳ ምድረ በዳዎች ወጥቶ የታየው (ማስተማር የጀመረው) ከሠላሳ ዘመኑ በኋላ ነበር። ሌላው ዓቢይ ምክንያት የሰው ሁሉ መጀመሪያ አባታችን አዳም የሠላሳ ዓመት ጎልማሳ ሆኖ ተፈጥሮ ተሰጥቶት የነበረው የልጅነት ጸጋ ለማስመለስ ሲል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሠላሳ ዘመኑ ተጠምቋል።
ጌታ በዮሐንስ እጅ የተጠመቀው ጥምቀት በዓለማም በመልዕክቱም ከዮሐንስ ጥምቀት ፍፁም ልዩ ነው። የዮሐንስ ጥምቀት ለጌታ ጥምቀት መንገድ የሚጠርግ ለጌታችን ጥምቀት ሕይወትን በንስሐ የሚያዘጋጅ የንስሐ ጥምቀት ነበር። "እኔ ለንስሐ በውሃ አጠምቃችኋለሁ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል። እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል" ማቴ 3÷11 የጌታ ጥምቀት ንስሐና ኑዛዜ፤ የእንስሳት ደምና መስዋዕት የሚያስፈልገው አልነበረም። የአዳምን ኃጢአት ለመደምሰስና ልጅነትን ለማስገኘት የተሰጠ ነው እንጂ። እስከ ሐዋርያት ትምህርት ድረስ የነበሩ ብዙ ሰዎች ያውቁት የነበረው የዮሐንስን ጥምቀት ነበር በዚህም የጸጋ ልጅነትን አላገኙበትም ነበር ይህ የተሰጠን በጌታችን ጥምቀት ነው። ዮሐ 3፥1

ጌታችን በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁ

ጠላት ዲያብሎስ በዮርዳኖስ የጣለውን የዕዳ ደብዳቤያችንን ለመደምሰስ፡- ብዙ ወንዞች ሳሉ ዮርዳኖስን መምረጡ በዮርዳኖስ ተጥሎ የነበረውን የዕዳ ደብዳቤያችንን ሊያጠፋ ነው። ቆላ 2፥14
ትንቢቱን ለመፈጸም ፡- "ባሕር አየች ሸሸች ዮርዳኖስም ወደ ኋላ ተመለሰች"..... ዮርዳኖስ ወደኋላ የተመለስከው ምን ሆነሃል.... "" መዝ 113÷5 መዝ 77÷16 መዝ 28፥3 የሚለውን ትንቢት ለመፈጸም ጌታ በዮርዳኖስ ተጠመቀ
ቀድሞ የተመሠለውን ምሳሌ አማናዊ ለማድረግ፡- ይኸውም ምሳሌ አንዲህ ነው
አብርሃም ነገሥተ ኮሎዶጎሞርን ድል አድርጎ ዮርዳኖስን ተሻግሮ መልከጸዴቅን አግኝቶ ኅብስተ አኮቴት ጽዋና በረከት ማግኘቱን ማቴ 14÷17
እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት መግባታቸውን ኢሳ 3÷14 ዕብ 7÷1
ኤልያስ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ወደ ብሔረ ሕያዋን ማረጉን 2ነገ 2÷8-14
ንዕማን በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ከለምጹ መፈወሱን 2ነገ 5÷14

ጌታ ለምን በሌሊት ተጠመቀ

በኃጢአት ጨለማ ለነበረ ሕዝብ የጽድቅ ብርሃን እንደወጣለትና በጨለማ የሚመሰል ኦሪት ይኖር ለነበረ ሕዝብ ብርሃን የሆነ ወንጌል መገለጡን ለማሳየት ነው። ኢሳ 9፥1 አንድም ጌታ ልደቱ፣ ጥምቀቱ፣ ትንሣኤው እንዲሁም ምጽአቱ በሌሊት ነው።

ይህም የሆነበት ምክንያት ሌሊትን ተከትሎ የሚመጣው ብርሃን በመሆኑ ከሞት ወደ ሕይወት፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከሲዖል ወደ ገነት የመሻገራችን ምሳሌ ነው። አንድም መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል የሚወርድ ነውና በጌታ ላይ የወረደው ርግብ እንጂ መንፈስ ቅዱስ ነው ባላሉ ነበር። በሌሊት ርግብ የለም ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ይታወቅ ዘንድ ነው።

ከዚሁ ጋር በተገናኘ መንፈስ ቅዱስ ለምን በርግብ አምሳል ወረደ ቢሉ እንዲህ እንመልሰለን። በኖኅ ዘመን ርግብ የጥፋት ውሃ ጎደለ ስትል የወይራ ዝንጣፊ ይዛ መጥታለች። መንፈስ ቅዱስም የኃጢአት ባሕር ጎደለ ሲል በርግብ አምሳል ወረደ። አንድም ርግብ ቢመቷት፣ እንቁላሏን ቢያበላሹባት ቤቷን ካላፈረሱባት በስተቀር ቦታዋን አትለቅም።

መንፈስ ቅዱስም ኃጢአት ሰርተው ፍፁም ካልካዱት በቀር ከፍጥረቱ አይለይም። አንድም ርግብ የዋሕ ናት ቂም በቀልም አትይዝም። መንፈስ ቅዱስም ኀዳጌ በቀል ይቅር ባይ ነውና በርግብ አምሳል ወረደ።
የጥምቀት ዓይነቶች፡- ጠቅለል ባለ መልኩ ሶስት የጥምቀት ዓይነቶች አሉ።

እነዚህም

ጥምቀት በደም ፡- በክርስቶስ አምነው ሳይጠመቁ ቆይተው በኋላ በሚፈጠር አጋጣሚ ወይም የቤተ ክርስቲያን ችግር ስለ ክርስቶስ እየመሰከሩ ሰማዕትነትን የሚቀበሉ ለእነዚህ ደማቸው ጥምቀት ሆኖ ያድናቸዋል። ማቴ 10፥32 ማቴ 20፥22 ሉቃ 12፥50

ጥምቀት በእንባ፡- በክርስቶስ አምነው የቤተ ክርስቲያን እምነት ተቀብለው በበደላቸው እያዘኑ እንባቸውን እያፈሰሱ ይቅርታን ሲለምኑ በቤተክርስቲያን ላይ በሚነሳ ችግር በውሃ የሚደረገውን ጥምቀት ሳይፈጽሙ ቢሞቱ እንባቸው እንደ ጥምቀት ይቆጠርላቸዋል። ስለዚህ በውሃና በመንፈስ ተጠምቀው ልጅነት አግኝተው የወረሱትን መንግስተ ሰማይ ይወርሳሉ። ነገር ግን ካህናት በማጣት እያለቀሰ (እያዘነ) ቆይቶ እግዚአብሔር ልመናውን ሰምቶ አጥማቂ ካህን ቢያገኝ አልቅሻለውና (አዝኛለውና) እንባዬ ጥምቀት ሆኖኛልና አልጠመቅም ማለት አይችልም ጥምቀት በውሃና በመንፈስ፡- ይህ በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመው አማናዊው ጥምቀት ነው። ዮሐ 3፥5

የሐዋርያት ጥምቀተ

ሐዋርያት መቼ ተጠመቁ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው ምላሽ በምሴተ ሐሙስ በአልዓዛር ቤት የሚል ነው። ጌታ ሐዋርያትን ሰብስቦ የቁርባንን ምሥጢር በገለጠላቸው በዛች ዕለተ ሐሙስ ከሁሉ አስቀድሞ እግራቸውን ባጠባቸው ጊዜ በአንድ ንባብ ሁለት ምሥጢር አስተማራቸው። ዮሐ 13፥4-15 ጥምቀት እና ትህትናን። ወዲህም ደግሞ ከጥምቀት በኋላ ልጅነት የሚጸናበትን ዘለዓለማዊውን ማዕድ የሥጋ ወደሙን ነገር አመለከታቸው። ማቴ 26፥26 ማር 14፥22 ዮሐ 6፥51

የአይሁድ ጥምቀት

አይሁድ ለመንፃትና ለኃጢአት ሥርየት የሚጠቀሙበት ጥምቀት ነበራቸው። መጠመቅ ብቻም አልነበረም። እግዚአብሔር በረድኤት በሚገለጽባቸውና አማኒያን ተሰብስበው እግዚአብሔርን በሚያመሰግኑባቸው የተቀደሱ ቦታዎች ሁሉ ሰውነትንና ልብስን የማጠብ በእግዚአብሔር ቤት መገልገያ የሆኑ እቃዎችን ሁሉ አጥቦ ማንጻት ሥርዓትና ልማድ ነበራቸው ይህም የእግዚአብሔርም ፈቃድ ያለበት አሠራር ነበር። ወደ ቤተ እግዚአብሔር ከመቅረባቸውና ለተቀደሰው አገልግሎት ከመሰየማቸው አስቀድሞ እግሮቻቸውንና እጆቻቸውን የመታጠብ ሥርዓትም ነበራቸው። ሰውነታቸውን ከአፍአዊ (ውጫዊ) እድፍ ንፁህ በማድረግ በባሕርዩ ንፁሕና ቅዱስ በሆነው አምላክ ፊት ውስጣዊ ሕይወትን ንጹሕ አድርጎ የመቅረብን ምሥጢር የሚያመላክት ነበር።

እኛስ ለምን እንጠመቃለን ቢሉ?

በጥምቀት ድኅነት እናገኛለን ማር 16፥16
- ከውሃና ከመንፈስ ዳግመኛ እንወለዳለን። የመጀመሪያው ልደት ከሥጋ ወላጆቻችን የምንወለደው ሥጋዊ (አካላዊ) ልደት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በጥምቀት የሚገኘው መንፈሳዊ ልደት ነው ዮሐ 3፥3-6 ቲቶ 3፥5 ኤፌ 5፥26

በጥምቀት ከጌታችን ሞቱን በሚመስል ሞት እንሞታለን፤ ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ እንነሳለን ቆላ 2፥12 ሮሜ 6፥3
የኃጢአት ሥርየት እናገኛለን። እምነት መሠረት ነው። ፍፁም የሚሆነው ግን በጥምቀት ነው ሐዋ 2፥38 ሐዋ 22፥16 “ኃጢአት በሚሠረይበት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን” ጸሎተ ሃይማኖት
አዲስ ሕይወት እናገኛለን። ያደፈው ሰውነታችን ይታደሳል። ይቀደሳል ሮሜ 6፥4
በጥምቀት የቤተ ክርስቲያን አባል እንሆናለን በዘመነ ኦሪት የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመሆን መገረዝ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነበር፡ ፡ በዘመነ ሐዲስም ጥምቀት በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚገኝ ጸጋ ተካፋይ እንድንሆን ያደርጋል ቆላ 2፥11-13


የታቦታት ጥምቀተ ባሕር መውረድ

የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆኑት ታቦታት ከመንበራቸው ተነስተው ወደ ጥምቀተ ባሕር መውረዳቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላከ አማልክት፣ የጌቶች ጌታ፣ የነገስታት ንጉሥ ሲሆን ወደ ዮርዳኖስ ወርዶ በዮሐንስ እጅ መጠመቁን ለማዘከር እርሱ ማደሪያው የሆኑት ታቦታትም ከመንበራቸው ተነስተው ወደ ጥምቀተ ባሕር ይሄዳሉ።

ጌታችን መጥምቀ መለኮት ዮሐንስን አስጠርቶት ካለበት መጠመቅ ሲችል ወደ እርሱ ሄዶ መጠመቁም ሥርዓት ለማስተማር ነው ይህም ስመ እግዚአብሔር ከሚጠራበት መስዋዕት ከሚሰዋበት ከቤተክርስቲያን ሄዳችሁ ተጠመቁ ሲል ነው። አስጠርቶት ተጠምቆ ቢሆን ዛሬ መኪንንቱ መሳፍንቱ ከቤታችን መጥታችሁ አጥምቁን ባሉ ነበር ማቴ 3፥13-14 ጌታችን በዮርዳኖስ በመጠመቁ ዮርዳኖስን እንደቀደሰው ሁሉ ታቦታቱም ባህረ ጥምቀቱን ሊቀድሱ (ሊባርኩ) ይወጣሉ።

ቃና ዘገሊላ

ጌታ በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ ዕለቱን ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሄዷል፡አርባው ቀን ሲፈጸምም ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሷል ኢየሩሳሌም በገባ በሦስተኛው ቀን የገሊላ አውራጃ ክፍል በምትሆን በቃና ሰርግ ሆነ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም እና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በሰርግ ቤቱ ተገኝ የወይን ጠጅ ባለቀባቸውም ጊዜ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ በመለወጥ የመጀመሪያውን ተአምር አድርጓል ዮሐ 2፥1-12 ይህ ተአምር የተደረገው የካቲት 23 ቢሆንም አበው የውኃን በዓል ከውኃ ለማገናኘት ሲሉ በጥምቀት ማግስት ጥር 12 ቀን እንዲከበር ወስነዋል።




መቋጫ

በዓለ ጥምቀት በመላው የክርስትናን እምነት በሚከተሉ ሁሉ በደማቅ ሁኔታ ይከበራል በዓሉ የሚከበርበት መሠረታዊ ምክንያት ተመሳሳይ ቢሆንም የአከባበሩ ይዘት ግን እንደየ ሀገሩና ቦታው ሥርዓትና ትውፊት የተለያየ መልክ አለው በሀገራችንም የጥምቀት በዓል በአደባባይ ወጥተን በድምቀት ከምናከብራቸው በዓላት አንዱ ሲሆን የተደረገልንን ታላቅ የድኅነት ሥራ አብነት በማድረግ የሚከበር ነው።ነብዩ ሕዝቅኤል "ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለው እናንተም ትጠራላችሁ" ሕዝ 36፥25 እንዲል በቅዱስ መጽሐፉ ጥምቀት ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነፃ የምንወጣበት የሥላሴ ልጅነትን የምናገኝበት መሆኑን እያሰብን የቤተ ክርስቲያናችንን ሥርዓትና ትውፊት ጠብቀን በማስተዋል እና የተሰጠንን ጸጋ ጠብቀን ርስት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ በማስተዋል በዓሉን ልናከብር ይገባል።

ከበዓለ ጥምቀት ረድኤትና በረከት ያሳትፈን አሜን!

ቀሲስ ኃይለኢየሱስ ተመስገን



ፍሳት

" አስተርእዮ ማርያም "

አስተርእዮ ማለት መታየት፣ መገለጥ ማለት ነው። ቃሉ አስተርአየ ታየ፣ ተገለጠ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ነው። ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት በሥጋ የተገለጠበት(የታየበት) ፣ አንድነት ሦስትነቱም የተገለጠበት ወቅት በመሆኑ ከልደት በዓል እስከ ጥር መጨረሻ በሙሉ ዘመነ አስተርእዮ በመባል ይታወቃል። የእመቤታችን በዓለ ዕረፍት በዘመነ አስተርእዮ ውስጥ ስለሚከበር "አስተርእዮ ማርያም" ተብሏል።

ልቡናዋ በይኩነኒ የጸና ንጽሐ ሥጋ ፣ ንጽሐ ነፍስ ፣ ንጽሐ ልቡና አስተባብራ የያዘች ወላዲተ አምላክ ምንም እንኳን የአምላክ እናት ብትሆንም ሞተ ሥጋ ለሁሉም ዕጣ ፈንታ በመሆኑ በቃል መነገሩ በልብ መታሰቡ ከፍ ከፍ ይበልና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ተንሥኢ ወንዒ" የነፍሴ ደስታ የኾንሽ ውድ እናቴ ሆይ ተነሥተሽ ወደ እኔ ነዪ (መኃ ፪፥፲) ብሏታል። ሞታ ለማርያም የዐጽብ ለኩሉ

ቅዱስ ዳዊት "ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር" መዝ.፹፮፥፫ እግዚአብሔር ማህጸንሽን ከተማ አድርጎ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን የኖረብሽ ሆይ ስለ አንቺ የተነገረው የተደረገው ነገር ዕጹብ ድንቅ ነው እንዳለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት ሆና ማረፏ ይደንቃል። ታላቁ የቤተክርስቲያናችን አባት ቅዱስ ያሬድ ሞቷ የሚያስደንቅ መሆኑን «ሞትሰ ለመዋቲ ይደሉ ሞታ ለማርያም የዐጽብ ለኩሉ፤ ሞት ለማናቸውም ሰው ሁሉ የተገባ ነው የማርያም ሞት ግን ሁሉን ያስደንቃል» በማለት ገልጾታል።

ሞት በጥር ነሐሴ መቃብር

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ሞትና ትንሣኤ በነገረ ማርያም አበው እንደሚያስረዱት ዕረፍቷ በጥር ፳፭ እሑድ ነው ። አባቶቻችን በጾመ ፍልሰታ ውዳሴ ማርያም ቅዳሴ ማርያም ሲተረጉሙ የእረፍቷን ነገር እንዲህ ብለው ይተርካሉ።

የእረፍቷስ ነገር እንደምን ነው ቢሉ ስድሳ አራት ዓመት በዚህ ዓለም ኖራ ጥር ፳፭ በእሑድ ቀን ጌታ እልፍ አዕላፋት መላእክቱን አስከትሎ መጥቶ እናቴ ሆይ ከዚህ ዓለም ድካም ላሳርፍሽ መጣሁ አላት። ልጄ ሰማይና ምድር የማይወስኑህ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማህጸኔ ተሸክሜ በድንግልና ወልጄህ እሞታለሁን? አለችው። በሲያል የሚሰቃዩ ነፍሳትን አሳይቶ እናቴ ሆይ ሞትሽ ለእነዚህ ቤዛ ይሆንላቸዋል አላት። ከማርክልኝስ ይሁን አለችው። ቅድስት ሥጋዋን ከቅዱስ ነፍሷ ለይቶ በቃለ አቅርጉት በዝማሬ መላእክት አሳረጋት። ደቀመዛሙርቱንም ከያሉበት በደመና ጠቅሶ ካለችበት አድርሶ እመቤታችሁን ስጋዋን በክብር አሳርፉ አላቸው።

ሐዋርያት በአጎበር አድርገው ወደ ጌቴሰማኒ ይዘው ሲሄዱ አይሁድ ቀድሞ ልጇን ተነሳ ዐረገ እያሉ ሲያውኩን ይኖራሉ አሁን ደግሞ እሷን ተነሳች ዐረገች እያሉ ሊያውኩን አይደለምን በእሳት እናቃጥላታለን ብለው ተነሱ። ታውፋንያ የሚባል አይሁዳዊ ተራምዶ አጎበሩን ጨበጠው። መልአክ መጥቶ በሰይፍ ሁለት እጁን ቀጣው ከአጎበሩ ተንጠልጥሎ ቀረ። በድያለሁ ማሪኝ ብሎ ቢማጸናት እጁ ተመልሶለታል። ከዚህ በኋላ ዮሐንስን ጨምሮ በደመና ነጥቆ ከገነት አግብቶ ከዕፀ ሕይወት ሥር አኖራት።

ቅዱስ ዮሐንስን እንደምን ሆነች አሉት ከገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አለች አላቸው ቅዱስ ዮሐንስ አይቶ እኛ ሳናይ ብለው በነሐሴ መባቻ ጾም ጀመሩ ሁለት ሱባዔ ሲፈጸምም እሑድ አምጥቶ ሰጥቷቸው ቀብረዋታል በሶስተኛው ቀን ማክሰኞ "ከመ ትንሳኤ ወልዳ" እንደ ልጇ ተነሥታለች። ቅዱስ ቶማስ አልነበረም ደመና ጠቅሶ ከሀገረ ስብከቱ ሲመጣ ስታርግ አገኛት ቀድሞ የልጅሽን ትንሳኤ ሳላይ ቀረሁ ዛሬም ደግሞ ያንችን ትንሳኤ ሳላይ ቀረሁን ብሎ "ወፈቀደ ይደቅ እምደመናሁ" ከሀዘኑ የተነሳ ሊወድቅ ወደደ እመቤታችንም አይዞህ አትዘን እሊያ ትንሳኤዬን ዕርገቴን አላዩም አንተ አይተሃል ተነሣች ዐረገች ብለህ ንገራቸው ብላ የያዘችውን ሰበን ሰጥታ ሰደደቸው። ከዚህ በኋላ ሄዶ የእመቤታችን ነገር እንደምን ሆነ አላቸው አግኝተን ቀበርናት አሉት ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር ተው ይህ ነገር አይመስለኝም አላቸው። ቅዱስ ጴጥሮስ አንተ ልማድህ ነው አንተ ብቻ ተጠራጥረህ አትቀርም ሰውን ሁሉ ስታጠራጥር ትኖራልህ ብሎ ተቆጥቶ ወደ መቃብሩ ሄዶ ቢከፍተው አጣት ደንግጦ ቆመ ሐዋርያው ቶማስም አታምኑኝም ብዬ እንጂ እመቤታችንስ ተነሣች ዐረገች አላቸው የያዘውንም ሰበን ሰጣቸው ለበረከትም ተካፍለውታል። በዓመቱ ሐዋርያት ቅዱስ ቶማስ ትንሣኤሽን ዕርገትሽን አይቶ እኛ ሳናይ ብለው ጾም ጀመሩ በ፲፭ኛው ቀን እመቤታችንን መንበር አድርጎ ቅዱስ ጴጥሮስን ካህን ዘይትራድኦ ቅዱስ እስጢፋኖስን ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ በዚያው ላይ ቀድሶ አቁርቧቸዋል። ቤተክርስቲያንም ይህንን መታሰቢያ አድርጋ በየዓመቱ ታከብረዋለች።ሰአሊ ለነ ቅድስት

የኃጥአንን ለቅሶና ሐዘን አፀተሽ ስለአነርሱ ድኅነት (መጻን) ዕረፍትሽን በሀሴት የተቀበልሽ እመቤታችን ሆዩ ሐዋርያት በሱባዔ ትንሣዔሽን ለማየት በቅተዋልና እኛም በዓለ ዕረፍትሽን አክብረን ልጅሽ በሰጠሽ ቃል ኪዳን በቀኙ እንቀም ዘንድ ለምኝልን። አሜን።



ምሕዋር

ኦርቶዶክሳዊ ሰርግ -

/ገብረ እግዚአብሔር ኪደ/



ኦርቶዶክሳዊ ሰርግ ማለት ትንሽዋ ቤተ ክርስቲያን የምትመሠረትበት፣ የባልና የሚስት አንድነት በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ የሚጸናበት፣ ባለትዳሮች በአንድነት ድኅነታቸውን ለመፈጸም ሰማያዊ ጉዞአቸውን በይፋ የሚጀምሩበት መንፈሳዊ ሥርዓት ማለት ነው።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከግራኝ አሕመድ ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መጋባት የተለመደ አልነበረም። በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የነበረው ባሕላዊ የሰርግ ሥርዓቱ ስለ ነበረ፥ ብዙውን ጊዜ በሥርዓተ ተክሊል ይጋቡ የነበሩት ካህናት ናቸው። ጥቂቶች ደግሞ በባሕላዊ ሥርዓት ተጋብተው ከቆዩ በኋላ በአንድነት ይቈርባሉ። ይህ ኋለኛው ብዙውን ጊዜ በዕድሜ በገፉ ባልና ሚስት ይከናወን የነበረና አሁንም የሚከናወን ሥርዓት ነው። ይህ የሚኾንበት ምክንያትም ግራኝ አሕመድ በምእመናን ሕይወት ላይ ካመጣው አሉታዊ ተፅዕኖ በተጨማሪ እንዳይፋቱ ወይም ድጋሚ እንዳያገቡ በመፍራት ነው።

ይህም ብቻ ሳይኾን ያለ ካህን ፈቃድ ማግባት (ዕቁባት ማስቀመጥ)፣ በኾነ ባልኾነው ሚስት ከባሏ፥ ባል ከሚስቱ መፋታት፣ ከብዙ ሴቶች ብዙ ልጅ መውለድ፣ በአጠቃላይ ምእመናን በቤተ ክርስቲያን የሚፈጸመውን ምሥጢራዊ ተሳትፎ ማለት ንስሓንና ቊርባንን ተክሊልን እየረሱት መኼዳቸው ግራኝ አሕመድ ጥሎት የኼደው እስላማዊ ልማድ ነው። ስለዚህ ይህ ከላይ እንደ ተጠቀሰው እስላማዊ ልማድ መኾኑን ተገንዝበን ልናስተካክለው የሚገባን ሥርዓት ነው።

ጋብቻችንን እውነተኛና የክርስቲያን ጋብቻ የሚያደርገው ቅዱስ ቊርባን ነው። "አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ኹለት አይደሉም" እንደ ተባለ ባልና ሚስት፥ ከኹለት አካል አንድ አካል የምንኾነው በቅዱስ ቊርባን ነው (ማቴ.19፡6)። ክብር ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋእለ ስብከቱ፥ በአንድ መልኩ መንግሥተ ሰማያት "ለልጁ የሰርግ ድግስ ያደረገ ንጉሥን" እንደምትመስል የተናገረው (ማቴ.22፡1)፥ በሌላ መልኩ ደግሞ በቃና ዘገሊላ ሰርግ ቤት ተገኝቶ ውኃውን ወደ ወይን ለውጦ ለሙሽሮችና ለሰርገኞች መስጠቱ እውነተኛ ጋብቻና ቅዱስ ቊርባን የማይለያዩ መኾናቸውን በግልፅ የሚያስረዳን ነው (ዮሐ.2፡1-11)።

ቅዱስ ቊርባን በራሱ ሰርግ ነው፤ ሥጋችን ሥጋው አጥንታችን አጥንቱ የሚኾንበት ምሥጢር ነው። ሰርግም እንደዚሁ በሥጋ ወደሙ፡- "ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ሥጋዬ ናት" የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር እውን የሚኾንበት (ዘፍ.2፡23)፣ ከሥጋዊ አንድነት በላይ የመንፈስን አንድነትና ፍቅርን ገንዘብ የምናደርግበት ነው። በጋብቻችን ካህናት ከሌሉና ኹለታችን አንድ የምንኾንበትን ሥጋ ወደሙ ካልተቀበልን ይህ ምሥጢር አይፈጸምልንም።

ምሥጢረ ጥምቀት አንድን ሰው ከፍጥረታዊ ሰው ወደ መንፈሳዊ ወይም ወደ ቤተ ክርስቲያናዊ ሰው እንደሚያሳድገው፥ ቅዱስ ቊርባንም ለጋብቻ አዲስ ትርጉም እንዲኖረው ያደርገዋል (1ኛ ቆሮ.2፡14-15)።

ዛሬ ይህ በኹለት መንገድ የሚፈጸም ሲኾን፥ የመጀመሪያው ሥርዓተ ተክሊል ነው፤ ኹለተኛው ደግሞ ሥርዓተ መዓስባን ነው። ስለዚህ እንደየአለንበት ደረጃ፥ በዚህ መንገድ ትንሽዋን ቤተ ክርስቲያን መመሥረት ያስፈልጋል።

ከዚህ በፊት ያለዚህ ምሥጢር የተጋባን ከኾንን ደግሞ ዛሬ ይህን ካወቅንበት ጊዜ አንሥቶ፣ ንስሓ ገብቶ አብሮ በመቊረብ ይህን ሕይወት መጀመር እንችላለን። ዋናው ቁም ነገር ከዚህ በኋላ እንደ ፈቃዱ ለመጓዝ መወሰናችን ነውና። ስለዚህ አስቀድመን አበ ነፍስ እንያዝ፤ አባታችን በሚነግሩን መሠረትም ቀኖናችንን ጨርሰንና ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ተቀብለን ወደዚህ አሁን ወደምንናገርለት ሕይወት መግባት እንችላለን።

/ገብረ እግዚአብሔር ኪደ/


“ጥምቀት ከኃጢኣት የሚያነጻ ነው። የመታደስና
የአዲስ ልደት ምክንያት ነው።”
ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ
“ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለስርየተ ኃጢአት፡
ኃጢአት በሚሰረይባት በአንዲት ጥምቀት
እናምናለን!”
ሠለስቱ ምዕት
ዕግዚአብሔር ምስሌነ / Egziabher Meslene

ቅምሻ

በኢትዮጵያ የበዓለ ጥምቀት አከባበር ከጥንት ጀምሮ እንዴት ይተረካል?

መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

ኢትዮጵያ ሀገራችን ስለ ነገረ ጥምቀት የሰማችው ከሌላው ዓለም አስቀድማ ጌታችን ባረገ በጥቂት ወራት (በ34 ዓ.ም) ነው (የሐዋ 8፥26-39)፤ ይህም በዐል ከዘጠኙ ዐበይት በዐላት አንደኛው ሲሆን ጌታችን ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ስላመራ ይህንን ለማሰብ ታቦታቱ ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ያመራሉ።

ሊቀ ትጉኃን ኃይለ ጊዮርጊስ በጻፉት የነገረ ሃይማኖት መጽሐፍ ላይ በስፋት እንደጻፉት በኢትዮጵያ በዚህ መልኩ መከበር የተጀመረው ከ515-529 ዓ.ም ለ14 ዓመት ኢትዮጵያን በመሩት በአጼ ገብረ መስቀል ዘመን ሲሆን በጊዜው ቅዱስ ያሬድ የነበረበት ጊዜ በመሆኑ ከዝማሬው በመነሣት ታቦታቱ ጥር 11 ጠዋት ከመንበረ ክብራቸው ተነሥተው ወደ ባሕረ ጥምቀቱ አምርተው አመሻሹ ላይ ይመለሱ ነበር።

ከዚያም ከ1157-1197 ዓ.ም ድረስ ለ40 ዓመት ኢትዮጵያን በመራው በታላቁ ጻድቅ ንጉሥ በላሊበላ ዘመን በአንድ አካባቢ ያሉ አብያተ ክርስትያናት ታቦታቱ ባንድ ላይ እንዲያከብሩ ንጉሥ ላሊበላ ታላቅ መንፈሳዊ ዐዋጅን አሳውጆ በአንድ አካባቢ፣ ወረዳ፣ ያሉ በአንድ ላይ ማክበር ጀመሩ፤ በርሱ ዘመን የነበሩት ታላቁ ጻድቅ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በአክሱም፣ በጎንደር፣ በሸዋ፣ በአንኮበር፣ በመርጡለ ማርያም እየሄዱ ባሕረ ጥምቀቱን ባርከዋል።

በመቀጠልም ከ1245-1268 ዓ.ም ለ23 ዓመት ኢትዮጵያን በመሩት በዐጼ ይኩኖ አምላክ ዘመነ መንግሥት በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አሳሳቢነት ታቦታቱ በባሕረ ጥምቀት ሲውሉ ምእመናን በታላቅ ድምቀት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ እንዲውሉ መንፈሳዊ ዐዋጅ አሳወጁ።
በመቀጠል ከ1426-1460 ዓ.ም ለ34 ዓመት ኢትዮጵያን በመሩት በታላቁ ንጉሥ በዐጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥትም ንጉሡ ከሊቃውንት ጋር በመወያየት የበዐሉን ታሪክ ተከትሎ ታቦታቱ ጥር 10 ከመንበረ ክብራቸው ተነሥተው ወደ ባሕረ ጥምቀት እንዲወርዱና ጥር 11 እንዲመለሱ ተወሰነ።

ታቦተ ጽዮን በሄደችበት ሁሉ በረከትን ትሰጥ እንደነበር የአቢዳራን ቤት በበረከት እንደሞላች፤ የዮርዳኖስን ባህር እንደከፈለች፣ የኢያሪኮን ቅጽር እንዳፈረሰች፣ የፍልስጤማውያን ጣዖት ዳጎንን ቀጥቅጣ እንዳጠፋች ሀገሪቱ ትባረክ ዘንድ ርኩሳን መናፍስት ይርቁ ዘንድ ምድሪቱ በቃል ኪዳኑ ታቦታት ትቀደስ ዘንድ ታቦታቱ በመጡበት መንገድ እንዳይመለሱ ታላቅ ዐዋጅ አሳውጀው በዐዋጁ መሠረት ዛሬ ድረስ በደመቀ መልኩ በዓሉ እየተከበረ ይገኛል።

ከባሕር ማዶ ሰዎች ውስጥ ቼሩሊ በዐጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመን ቁመቱ 14 ወርዱ 8 ክንድ የኾነ ባሕረ ጥምቀት እንደተዘጋጀ ሲጽፍ፤ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዐጼ ልብነ ድንግል በተገኙበት እጅግ ታላቅ ድንኳን በባሕረ ጥምቀቱ ዙሪያ እንዴት ተተክሎ እንደተከበረ ፍራንቺስኮ አልቫሬዝ ገልጿል፤ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን የበዓለ ጥምቀት አከባበር ደግሞ ፔድሮ ፔየዝ ዘግቦት ነበር።

አሁን ባለንበት ጊዜም ዳዊት በመዝ 44፡16 ላይ "በአባቶችሽ ፋንታ ልጆች ተወለዱልሽ" በማለት እንደተናገረ ከመቼውም በበለጠ እግዚአብሔር የወጣቱን ልብ በረድኤት ጎብኝቶት ለቃል ኪዳኑ ታቦታት ክብር አካባቢውን እያስዋበ፣ ታቦታቱ የሚሄዱበትን መንገድ እየጠረገ፤ ታላላቅ ምንጣፎችን ታቦታቱ በሚሄዱበት መንገድ እያነጠፈ ለቃል ኪዳኑ ታቦት እንደ ነቢዩ ዳዊት ከፍተኛ ክብር በመስጠት እግዚአብሔርን እያገለገለ ይገኛል (1ኛ ነገሥት 6፡1-23)።

"የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ታቦትና ሌዋውያን ካህናት ተሸክመውት ባያችሁ ጊዜ፥ ከሰፈራችሁ ተነስታችሁ ተከተሉት"
(ኢያ 3፡3)
መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ



ዘክር



ጥር 28

እንኳን ለአባታችን ዐማኑኤል ዓመታዊ ክብረ በዓል በሰላም አደረሳችሁ

††† ተአምራተ እግዚእ †††

ጌታችን በመዋዕለ ስብከቱ ብዙ ተአምራትን ሰርቷል። እያንዳንዱ ግን ቢጻፍ ዓለም በራሷ ባልበቃች ነበር። ከእነዚህ መካከልም አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌው በዚህ ዕለት በ7 እንጀራ እና በጥቂት ዓሣ ሴቶችና ሕፃናትን ሳይጨምር 4ሺ ወንዶችን በቸርነቱ አበርክቶ አጥግቡዋል። ደቀ መዛሙርቱም 7 ቅርጫት ማዕድ አንስተዋል::ጌታችን በከሃሊነቱ የተራቡትን ሲያጠግብ እንዲሁ አይደለም። በጊዜው የነበሩ አይሁድ ጠማሞች ነበሩና እነሱን ምላሽ በሚያሳጣ መንገድ ነበር እንጂ:: አይሁድ ላለማመን ብዙ ጥረት ነበራቸውና።በዚህ ዕለትም እንጀራ አበርክቶ ሲያበላቸው:-

1.ጊዜው አመሻሽ ላይ ነበር። ምክንያት:- ጧት ላይ ቢሆን ከቤታችን የበላነው ሳይጎድል ብለው ከማመን ይርቁ ነበርና።

2.ከውሃ ዳር አድርጎታል። መታጠቢያ ብናጣ በደንብ ሳንበላ ቀረን እንዳይሉ።

3.ሳር የበዛበት ቦታ ላይ አድርጎታል። ምክንያቱም መቀመጫ ብናጣ በደንብ ሳንበላ ቀረን እንዳይሉ።

4.ከከተማ አርቆ ምድረ በዳ ላይ አድርጎታል። ያማ ባይሆን "ፈጣን ፈጣን ደቀ መዛሙርቱ ተሯሩጠው እየገዙ አቀረቡለት" ባሉ ነበርና።

ለመድኃኒታችን ክርስቶስ አምልኮና ምስጋና ይሁን! ዐማኑኤል አምላካችን ጣዕመ ፍቅሩን ያሳድርብን::

"ጌታ ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ ሕዝቡ ከእኔ ጋር እስከ አሁን ሦስት ቀን ውለዋልና የሚበሉት ስለሌላቸው አዝንላቸዋለሁ። በመንገድም እንዳይዝሉ ጦማቸውን ላሰናብታቸው አልወድም አላቸው። ደቀ መዛሙርቱም ይህን ያህል ሕዝብ የሚያጠግብ ይህን ያህል እንጀራ በምድረ በዳ ከወዴት እናገኛለን? አሉት። ጌታ ኢየሱስም ስንት እንጀራ አላችሁ? አላቸው።

እነርሱም "ሰባት ጥቂትም ትንሽ ዓሣ" አሉት። ሕዝቡም በምድር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ። ሰባቱንም እንጀራ ዓሣውንም ይዞ አመሰገነ። ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጠ። ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ። ሁሉም በሉና ጠገቡ። የተረፈውንም ቁርስራሽ ሰባት ቅርጫት ሙሉ አነሱ። የበሉትም ከሴቶችና ከልጆች በቀር አራት ሺህ ወንዶች ነበሩ።" (ማቴ. 15:32)

ወስብሐት_ለእግዚአብሔር

ጥቆማ



ርዕስ - ትንሿ ቤተ-ክርስቲያን

ጸሐፊ - ገብረ እግዚአብሔር ኪደ

የጀርባ ዋጋ 6ተኛ እትም - 1080 ብር

የገጽ ብዛት - 567

ከመጽሐፉ የተወሰደ

• ጌታችን ክርስቶስ፡- "ተፈጸመ" እንዳለው፥ ባልም እስከ ሞት ድረስ፣ እስከ ንዝንዙ ፍጻሜ መድናት አለበት። እንደዚህ በሚኾንበት ጊዜ ባል፡- "ከእንግዲህ ወዲህ ሚስቴን የምወድዳት እኔ አይደለሁም፤ ክርስቶስ በእኔ ይወድዳታል እንጂ" ማለት ይችላል።

© ትንሿ ቤተ ክርስቲያን፣ ገጽ 320